# “አሁን እየተሰራ ያለው የአማተሮች ትያትር ነው”

**አቶ ልደቱ አያሌው**

ጥቅምት /11/2013 ዓ.ም

ላለፉት ሶስት ወራት በእስር ላይ የሚገኙት አቶ ልደቱ አያሌው፤ ፖሊስ ህገ መንግስቱን ጥሶ ሊፈታቸው ባለመፍቀዱ በፍርድ ቤት በዋስትና ጉዳይ ላይ ያለው ክርክር ቀርቶ ሌላው የፍርድ ሂደት እንዲቀጠል ጠየቁ። የፍርድ ቤት ውሳኔን ሳያስፈጽሙ የቀሩ አካላትን በተመለከተ “አሁን እየተሰራ ያለው የአማተሮች ትያትር ነው” ሲሉ እርምጃቸውን አጣጥለዋል።

ያስያዙት የ100 ሺህ ብር ዋስትና ተከብሮላቸው ከእስር ሳይለቀቁ የቀሩት አቶ ልደቱ፤ በዛሬው የችሎት ውሎ ጠንከር ባለ ጽምጸት በጉዳዩ ላይ ያላቸውን አቋም አንጸባርቀዋል። የዞኑ ፍርድ ቤት የህግ የበላይነትን ለማስከበር አቅሙ የፈቀደውን ያህል ላደረገው ጥረት አክብሮታቸውን የገለጹት ዕውቁ ፖለቲከኛ፤ የፍርድ ቤቱን “ውድ ጊዜ”፣ እርሳቸው “ትያትር” ሲሉ በጠሩት ድርጊት ማባከን እንደማይፈልጉ አስታውቀዋል።

“ከዚህ በኋላ ለታሪክ፤ ፖሊስ ሕገ መንግስቱን ጥሶ፣ የእኔንም መብት ጥሶ ያለከልካይ መሆኑ ይመዘገብልኝና ወደ ሌላው ክርክር እንቀጥል። ይሄ ጨዋታ ይቁም። እኔ የፍርድ ቤቱን ጊዜ በዚህ ማባከን አልፈልግም። እናንተ የምትችሉትን ሁሉ አድርጋችኋል። ከዚህ በላይ አልጠብቅም” ሲሉም ለፍርድ ቤቱ ተናግረዋል።